የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በስድስት ዞኖች (በጋሞ፣ በጎፋ፣ በዎላይታ፣ በጌዴኦ፣በኮንሶና፣ በደቡብ ኦሞ) እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች (በቡርጂ፣በአማሮ፣ በዲራሼ፣ በባስኬቶ እና በአሌ) የተከናወነው ህዝበ-ውሣኔ አፈፃፀም ማጠቃለያ ሪፖርት

## (Summary Report)

ሰኔ 2015 ዓ/ም

# በስድስት ዞኖች እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች ጥር 29 ቀን 2015 ዓ/ም የተካሄደው ህዝበ ውሣኔ  እና ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ/ም በዎላይታ ዞን   የተካሄደው የድጋሚ ህዝበ ውሣኔ አፈጻጸም መግለጫ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በቁጥር ፌደም/አፈ/ም/80 2011 በቀን 12/12/2014 በተፃፈ ደብዳቤ መሠረት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ስር በስድስት ዞኖች  ማለትም በጋሞ፣ ጎፋ፣ ዎላይታ፣ ጌዲዮ፣ኮንሶና፣ ደቡብ ኦሞ እና  በ አምስት ልዩ ወረዳዎች  ማለትም ቡርጂ፣አማሮ፣ዲራሼ፣ ባስኬቶ እና አሌ ላይ የህዝበ ውሣኔ  አካሂዶ ውጤቱን እንዲያሳውቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን መጠየቁ የሚታወስ ነው። በዚሁ መሰረት ጥር 29 ቀን 2015 ዓ/ም የተካሄደው ህዝበ ውሣኔ  እና ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ/ም በዎላይታ ዞን   የተካሄደው የድጋሚ ህዝበ ውሣኔ አፈጻጸም እና ውጤት በተመለከተ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

## የጥር 29 ቀን  2015 ዓ/ም የህዝበ ውሣኔ አፈጻጸም

### 1. የቅድመ ዝግጅት ተግባራት

ቦርዱ በስድስት ዞን እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች ህዝበ ውሣኔውን ለማስፈፀም በ6ኛው የጠቅላላ ምርጫ ስራ ላይ  ከዋሉት 2900 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ 10 በመቶ በመጨመር በጠቅላላው 3542 የምርጫ ጣቢያዎች አደራጅቶ 3,106,585 (ሶስት  ሚሊዮን አንድ መቶ ስድሰት ሺ አምስት መቶ ሰማኒያ አምስት ) የሚጠጋ መራጭ ሕዝብ በመራጭነት ይመዘገባል ብሎ በመገመት ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈጸም በማቀድ ተንቀሳቅሷል።

ለህዝበ ውሣኔው ስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች ፣ 31 ማእከላት፣ እና 3542 የምርጫ ጣቢያዎችን መሰረት አድርጎ ለምርጫ አስፈፃሚዎች የሚከፈል ደመወዝ ፣ የውሎ አበል፣ ነዳጅ፣ ለምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና የሚያስፈልግ ወጪ ፣ ለህዝበ ውሣኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እና የሚታተሙ ሰነዶች፣ በዓይነትና በብዛት በመዘርዘር እንዲሁም በዕቅዱ ለመጋዘን ኪራይ የሚያስፈልግ ወጪ   በዝርዝር የማዘጋጀት ስራ አከናውኗል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ለህዝበ ውሣኔ ማስፈፀሚያ አጠቃላይ  የታቀደው የተስተካከለ በጀት ብር **470,421,770.50** (አራት መቶ ሰባ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ከ50/100) ተዘጋጅቶ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ ስራ ላይ ውሏል።

### 2. በየደረጃው የሚገኙ ጽ/ቤቶችን ማደራጀት

ቦርዱ ህዝበ ውሣኔው በተሳካ እና በተቀናጀ አሰራር ለማከናወን ለሕዝበ ውሣኔው ማስፈጸሚያነት የሚያገለግሉ ጽ/ቤቶች እና መጋዘኖች በየደረጃው ያቋቋመ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት የዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በአርባ ምንጭ ከተማ ፣ የስድስት ዞኖችና የአምስት ልዩ ወረዳዎች የዞን ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን እና እና መጋዘኖች በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ፣ 31 የሕዝበ ውሣኔ ማስተባበሪያ ማዕከላት ጽ/ቤት እና መጋዘኖች እና  በ3,771 የምርጫ ጣቢያዎች ጽ/ቤቶችን አደራጅቷል።

### 3. የህዝበ ውሣኔ ማስፈጸሚያ መመሪያ ማዘጋጀት

በርዱ ህዝበ ውሣኔውን ለማስፈጸም የሚረዳ የሕዝበ ውሣኔ አፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ፡ የተዘጋጀው መመሪያ በስራ አመራር በርዱ ተመርምሮ፣ ማሻሻያ ተደርጎበትና ፀድቆ በስራ ላይ ውሏል። መመሪያው በርዱ የሕዝበ ውሣኔውን ጥያቄ በህግ እና በመመሪያ ማስፈጸም እንዲቻል እንዲሁም ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈጸም የሚያደራጃቸውን ቢሮዎች አይነት፣ የስራ ድርሻ፣ ተጠያቂነት እንዲሁም በነዚህ አደረጃጀቶች መካከል የሚኖረውን የስራ ግንኙነት፣ የመረጃ ልውውጥ እና ሪፖርት አደራረግ በግልጽ የሚያስቀምጥ ነው፡ ፡

### 4. ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር እና ውይይት

በርዱ የህዝበ ውሣኔው ኦፐሬሽናል እቅድ እና የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከክልሉ መንግስት፣ ከዞኖችና ከልዩ ወረዳዎች የመስተዳድር አካላት እንዲሁም ከፌደራልና የክልል ፀጥታ መ/ቤቶች ጋር የተለያዩ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ጠቃሚ ግብአት የወሰደ ሲሆን በተለይም ክክልሉ መንግስት አስተዳዳር አካላት፣ ከዞን እና ልዩ ወረዳ አመራሮች ፣ ከክልሉ እና የዞን እና ልዩ ወረዳ የጸጥታ አካላት ጋር በጸጥታ ጉዳይ እና በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዲሁም ከመንግስት አካላት ስለሚጠበቁ ሀላፊነቶች በተደጋጋሚ በአርባ ምንጭ ከተማ ውይይቶች አድርጓል።

### 5. የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ

በርዱ ለህዝበ ውሣኔ አፈጻጸም በዞን ፣ በህዝበ ውሣኔ ማእከላት እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ለመመልመል እንዲያስችለው በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ የተሣተፉና ሕዝበ ውሣኔው ላይ ለመሣተፍ ፍላጎት ላላቸው ጥሪ በማድረግ የመምረጥ ስራ የተሰራ ሲሆን የተመረጡትን አስፈጻሚዎች ገለልተኛነት ለማረጋገጥ ሕዝብ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ዝርዝራቸው በኦንላይን ይፋ ተደርጓል። በዚህም ባለድርሻ አካላት በአስፈጻሚዎቹ ገለልተኝነት ላይ ባቀረቡት ተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ማስተካከያ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት ጥር 29 በተካሄደው ህዝበ ውሣኔ በ6 ዞን እና 5 ልዩ ወረዳዎች 38 የዞን አስተባባሪዎች ፣ በ31 ማእከላት 135 የማእከል አስተባባሪዎች እና በ3771 የምርጫ ጣቢያዎች **17250** የምርጫ አስፈጻሚዎች ተመልምለው ውል በማስገባት በህዝበ ውሣኔው ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

### 6. የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና

በምርጫ ስርአቱ ውስጥ የዜጎችን የመምረጥ መብት፤ የሴቶችን እና አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የምርጫ በርድ የስልጠና ክፍል ልዩ ልዩ ተግባራትን አከናውናል። ከእነዚህም ተግባራት መካከል በተለያየ ደረጃ በምርጫ አስፈጻሚነት የሚሳተፉ አካላት፤ የምርጫ ህጉን በአግባቡ እንዲረዱ፤በምርጫ ተግባራት ላይ ስለሚኖራቸው ሚና፤ እና

የመራጮች ምዝገባ ሂደት፤ እንዲሁም የድምጽ አሰጣጥ ውጤት ቆጠራ እና ይፋ አደራረግ ላይ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው፤ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ለተሰጡ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ብር **112,518,110.00** ጸድቆ ወደስራ ተገብቷል፡፡

አሰልጣኞችን በተመለከተ የመሪ እና ዋና አሰልጣኞች ከምርጫ ቦርድ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች እንዲሁም ከአጋር ድርጅት ባለሙያዎችን በማሳተፍ የትውውቅ ስልጠና በመስጠት ዝግጅት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም በተቀመጠው የስልጠና እቅድ መሰረት፤ በመራጮች ምዝገባ እንዲሁም፤ በድምጽ አሰጣጥ እና ውጤት ቆጠራ ለ10 መሪ አሰልጣኞች ስልጠናው በአዲስ አበባ የተሰጠ ሲሆን ለመራጮች ምዝገባ ለ**299** የመስክ አሰልጣኞች እንዲሁም ለድምጽ አሰጣጥ ቀን እና የውጤት ማደመርና ይፋ የማድረግ ለ**246** የመስክ አሰልጣኞች በአርባ ምንጭ ከተማ በተዘጋጀ የስልጠና ማእከል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

እነዚህ የመስክ አሰልጣኞችም በ**6** ዞኖች እና **5** ልዩ ወረዳዎች ውስጥ በተቋቋሙ 11 የማስተባበሪያ ማእከላት ስር በመሰማራት የምርጫ አስፈጻሚዎችን አሰልጥነዋል፡፡ በዚህም መሰረት፤ ለመራጮች ምዝገባ፤ **ለ11,082** የምርጫ አስፈጻሚዎች እንዲሁም፤ ለድምጽ አሰጣጥ ቆጠራ እና ውጤት ይፋ አደራረግን ደግሞ **ለ11,175** የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## 7. የምልክት መረጣ

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስድስቱ ዞኖች (ኮንሶ፣ ዎላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጋሞ፣ ጌዴኦ፣ ጎፋ) እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች (ቡርጂ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ እና ዲራሼ) በአንድ ክልል መደራጀታቸውን አልደግፍም ለሚለው  የሕዝበ ውሣኔ አማራጭ ሃሣብ ምልክት« **ጎጆ ቤት**» የተመረጠ ሲሆን እንደዚሁ ደግሞ "በአንድ የጋራ ክልል መደራጀታቸውን እደግፋለሁ" ለሚለው ሀሳብ ምልክት «**ነጭ ዕርግብ**» ሆኖ ተመርጦ በዚሁ መሰረት የድምጽ መስጫ ወረቀት የማዘጋጀት ስራ ተከናውኗል፡፡

## 8. የህትመት ፣ ቁሳቀስ ግዢ እና ክምችት

ለመራጮች ምዝገባ ስልጠና እና ለመራጮች ምዝገባ ኦፕሬሽናል ፣ ለ ህዝበ ውሣኔ ቀን ስልጠና እና ህዝበ ውሣኔ ቀን ኦፕሬሽናል ስራ የሚረዱ የጽህፈት መሳሪያዎችን የያዙ ኪቶች ግዢ ከቻይና የተፈጸመ ሲሆን የመራጮች መዝገብ፣ ካርድ፣ ጣት ላይ የሚቀባ የማይጠፋ ቀለም፣ እና የተለያዩ በመራጮች ምዝገባ በህዝበ ውሣኔ ቀን ጥቅም ላይ የሚውሉ ቅጾች እንዲሁም 4,040,000 የድምጽ መስጫ ወረቀቶች አለም አቀፍ ግዢ በቦርዱ አጋር ማለትም በተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት አማካይነት ከዱባይ ተፈጽሟል።

ጥር 29 ቀን ለተከናወነው ህዝበ ውሣኔ ለስልጠና እና ለኦፕሬሽን ስራዎች የዋሉ ህትመቶች እና ኪቶች ግዢ የዋለው ገንዘብ መጠን 82,319,310 (ሰማኒያ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺ ሶስት መቶ አስር ብር ) ሆኗል። ለሕዝበ ውሣኔ ማስፈፀሚያ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሰነድ እና ቁሳቁሶች ከሀገር ውጪ ታትመው በሚመጡበት ወቅት ሰነድ እና ቁሳቁሶቹን በጥያቄው መሰረት በትክክል እና በጥሩ ሁኔታ፣ ደህንነቱን እና ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ መንገድ መድረሳቸውን የማመሳከር እና የመረከብ ስራ እንዲሁም ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ በማሳጀብ በመጋዘን የማከማቸት ስራ ተከናውኗል።

## 9. እሽጋ፣ ድልድል እና ስርጭት

ለህዝበ ውሣኔው ለመራጮች ምዝገባ፣ ለድምፅ አሰጣጥ ሂደት እና ውጤት ማዳመሪያ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሰነድ እና ቁሳቁሶችን ለስልጠና እና ኦፕሬሽን በተገቢው መንገድ ከነመጠባበቂያው በማሸግ በፌደራል ፖሊስ በማሳጀብ ወደ 6ዞን እና 5 የልዩ ወረዳዎች እንዲሁም 31 ማዕከላት የተሰራጨ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ ከማእካለት ወደ ምርጫ ጣቢያ በጊዜ ሰሌዳው መሰረት በክልሉ እና ዞኑ ፖሊስ በማሳጀብ ተሰራጭቷል። ። የእሽጋ እና ስርጭት ስራ በሶስተኛ ወገን ሰራተኞች ከቦርዱ የሎጅስቲክስ ሰራተኞች ጋር በመቀናጀት ተከናውኗል።

## 10. የህግ ክፍል ስራዎች

ቦርዱ ጥር 29 ቀን 2015 ዓ/ም በተካሄደው ህዝበ ውሣኔ የቅሬታ አፈታት መዋቅር ዝርጋታን በሚመለከት በመጀመሪያ አግባብነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎች በቦርዱ ፀድቀው ስራ ላይ የሚገኙ መመሪያዎች ላይ ጥልቅ ፍተሻ በማድረግ አወቃቀሩ በየትኛው የእርከን ደረጃ ተፈፃሚ ሊደረግ ይችላል የሚለውን ውይይት በማድረግ ቅሬታ አፈታት መዋቅሮቹ በስድስቱ ዞኖች እና በአምስቱ ልዩ ወረዳዎች የህዝበ ውሣኔ ማስተባበሪያ ቢሮዎች ደረጃ እንዲዋቀሩ ተደርጓል። እንዲሁም ቦርዱ ከደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ለተወጣጡ የፖሊስ አባላት በምርጫ የህግ ማዕቀፎች ፣የምርጫ ፀጥታ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲሁም የምርጫ አዋጁ በተለይም ከህዝበ ውሣኔ አንፃር ምርጫ ቦርድ ያወጣው በምርጫ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቶች የተመደቡ የፀጥታ አካላት አሰራር ደንብ እና ስነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 12/2013 በተመለከተ ስልጠና ተሰጥ□ል። እንዲሁም የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን በህዝበ ውሣኔ የክልሉ ፖሊስ ሚናን የሚመለከት ዝርዝር የአሰራር መመሪያ አቅርቧል። በስልጠናው የተሸፈኑት ርዕሰ ጉዳዮች የምርጫ ነክ ወንጀሎችን የሚመለከቱ አለም አቀፍ ልምዶች፣ የምርጫ ነክ ወንጀሎች በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት እንዲሁም የምርጫ ነክ ወንጀሎች

ምርመራ መሰረታዊ መርሆዎችና ክህሎቶች ናቸው። የምርጫ ነክ ወንጀሎች ምርመራ መሰረታዊ መርሆዎችና ክህሎቶች ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርቲ በመጡ አሰልጣኞች ተሰጥቷል።

## 11. የውጭ ግንኙነት ስራዎች

በርዱ ህዝበ ውሣኔውን መታዘብ ለሚፈልጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ ጥሪ በማድረግ ህዝበ ውሣኔውን ለመታዘብ ማመልከቻ ያስገቡ 9 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ያቀረቧቸውን ተያያዥ ሰነዶች በአዋጁ እንዲሁም በመመሪያ 05/2012 ዓ.ም ከተቀመጡት መስፈርቶች አንፃር ማሟላታቸውን ገምግሞ፣ 6ቱ ተቀባይነት ያገኙ ቢሆንም ከእነሱ ውስጥ 3ቱ በበጀት እጥረት ለመታዘብ ባለመቻላቸው ለቀሩት 3ቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማለትም 1ኛ). የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ፣ 2ኛ). የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) እና 3ኛ). የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ፌዴሬሽን አመልክተው፣ተገምግመው እና እውቅና አግኝተው፤ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ 510 ፣ ኢ.ሰ.መ.ጉ 22፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ፌዴሬሽን 915 በጥቅሉ 1,447 ታዛቢዎችን ያሰማሩ ሲሆን በርዱ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር ታህሳስ 13 2015 ዓ/ም በምርጫ ወቅት ስለሚካሄድ የሰብአዊ መብቶች ክትትልን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ በተፈራረመው መሰረት 64 የሰብዓዊ መብቶች ተከታታዮችን አሰማር□ል።
በመሆኑም በአጠቃላይ ሲቪል ማህበራቱ እና ኢ.ሰ.መ.ኮ በአንድነት 1,511 የሰው ሀይል አሰማርተው 1,890 የምርጫ ጣቢያዎችን ለመሸፈን ችለዋል።

ሕዝበ ውሣኔውን ለመታዘብ በቦርዱ ፍቃድ የተሰጣቸው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ወደመስክ ለሚያሰማሩዋቸው ታዛቢዎቻቸው የሚሰጡትን የቅድመ መታዘብ ስልጠና የክትትል ስራ ከመሰራቱም ባሻገር፤ ለስልጠናው አጋዥ የሆነ የመመሪያ ቁጥር 05/2012 ዓ.ም የማሰልጠኛ ማኑዋል በማቅረብ፤ የሞያ እና የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጓል።

## 12. የመራጮች ትምህርት

በርዱ በህዝበ ውሣኔው የሚሳተፉ መራጮች ግንዛቤ እንዲያገኙ ለመራጮች ትምህርት ወይም መረጃ የሚሰጡ ስድስት የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎች (PSAs) ተዘጋጅተው በኢቲቪ፣ ፋና ፣ እና ደቡብ ቲቪ ተላልፈዋል። የማስታወቂያዎቹ የድምጽ ቅጂ በ20 የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ተተርጉመው በዘጠኝ ብሔራዊ፣ ክልላዊ እና የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች ተላልፈዋል። የማስታወቂያዎቹ ይዘቶች የምርጫ ቅስቀሳ፣ የ□ታ እኩልነት እና ማህበራዊ አካታችነት እና አጠቃላይ የመራጮች መረጃዎችን ያካተቱ ነበሩ።

በህዝበ ውሣኔው ዙርያ ለመራጮች መልዕክት እና መረጃ የሚሰጡ ፖስተሮች ሁለት አይነት ሲሆን የአንደኛው ፖሰተር ይዘት መራጮች በምርጫ ወቅት የድምጽ መስጫ ወረቀትን በምን አይነት መልኩ መጠቀም እንዳለባቸው የሚያስረዳ ሲሆን ሁለተኛው ፖስተር ደግሞ መራጮች ወደምርጫ ጣቢያ ሲመጡ

መፈጸም ያለባቸውን መሰረታዊ ክንዋኔዎች ደረጃ በደረጃ የሚተነትን ነው። ለሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ከእያንዳንዱ ፖስተር ሁለት ሁለት ተሰራጭተዋል።

ቦርዱ የተለያዩ የመገናኛ አውታሮችን በመጠቀም ከሚሰጣቸው መረጃዎች እና የተለያዩ የሕዝብ ማስታወቂያዎች (PSAs) በመጠቀም ከሰጣቸው የሕዝበ ውሣኔው ተኮር አጫጭር መረጃዎች በተጨማሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጥሪ በማድረግ የመራጮች ትምህርት ፈቃድ በመስጠት በዞኖቹ እና በልዩ ወረዳዎቹ የመራጮች ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች እና የተለያዩ ቋንቋዎችን በመጠቀም ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል። ቦርዱ የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፍላጎት እና አቅም ላላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ያደረገውን ጥሪ ተከትሎ ማመልከቻ ካስገቡት ከ50 በላይ ከሚሆኑ ድርጅቶች መካከል ለ29 ድርጅቶች ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀረቡ 14 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶ የመራጮች ትምህርት በመስጠት ተሳትፈዋል። ቀሪዎቹ ግን በተለያዩ ምክንያቶች፣ በዋናነት ለመራጮች ትምህርት የሚሆን በጀት ማግኘት ባለመቻላቸው የመራጮች ትምህርት መስጠት አልቻሉም።

ከዚህ በተጨማሪ በሂደቱ የአካታችነት መርህን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻልና ሁሉም ዜጎች ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማድረግ ህዝበ ውሣኔው በሚካሄድበት አካባቢ የተደራሽነት ችግር ላለባቸው ማለትም ለሴቶች፤ለአካል ጉዳተኞች ፤ ልዩ ምርጫ ጣቢያዎች በተቋቋመባቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች በሚገኙበት አካባቢ መስራት ለሚፈልጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ መስፈርቶች በማውጣት ለሦስት ድርጅቶች የደቡብ መምህራን ማህበር ጽ/ቤት፣የደቡብ ኢትዮጵያ የሲቪክ ማህበራት ጥምረት እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ለያንዳንዳቸው የሁለት መቶ አምሳ ሺህ (250000) ብር ድጋፍ አድርጓል።

## 13. የተደረገ ክርክር

በህዝበ ውሣኔው ላይ በአዲስ አበባ፣ በሀዋሳ እና በአርባ ምንጭ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከምሁራን የተወጣጡ ከህዝበ ውሣኔው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ባላቸው ግለሰቦች መካከል ክርክሮች ተካሂደዋል። በአዲስ አበባ የተካሄደው ክርክር በአርትስ ቲቪ ተቀርጾ ተላልፏል። ክርክሩን የመሩት **Center for Advancement of Rights and Democracy (CARD) ነበሩ ሁለተኛውን እና** በሀዋሳ የተካሄደው ክርክር ደግሞ በደቡብ ቲቪ ተቀርጾ ለተመልካች የተላላፈ ሲሆን ክርክሩን የመሩት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ) ሲሆኑ ሦስተኛው ክርክር በአርባ ምንጭ ከተማ በቀጥታ ታዳሚ በተገኙበት በመምህራን ኮሌጅ አዳራሽ የተካሄደ ሲሆን በአርትስ ቲቪም ክርክሩ ተቀርጾ ተላልፏል። ይህንን ውይይት የመሩት ሀበጋር ዲቤትስ ናቸው።

## 14. የኮምዩኒኬሽን ስራዎች

የኮምዩኒኬሽን ክፍል ህዝበ ውሣኔውን የተመለከቱ የተለያዩ ውሣኔዎችን በቦርዱ የማኅበራዊ ትሥሥር ገጽ ላይ ለማጋራት በሚመች መልኩ ዐርትዖት በመሥራት፣ መግለጫዎች ማስታወቂያዎችና የተለያዩ ጥሪዎችን ማስተላለፍ እንዲሁም በቦርዱ የኮምዩኒኬሽን ማንዋል መሰረት እርምቶችን የመስራት ስራዎች ተሰርተዋል።

በዋናነት ከተለያዩ ሚዲያዎች የሚመጡ ሕዝበ ውሣኔው ላይ የሚያተኩሩ ጥያቄዎችን በመቀበል ለሚመለከታቸው አካላት በማስተላለፍ ሚዲያዎቹ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ የማድረግ ስራ የተሰራ ሲሆን በዚህም ስፋት ያላቸው ሚዲያዎች ተስተናግደው በቂ የሆነ ምላሽ አግኝተዋል ። ይህንንም ተከትሎ የተለያዩ ዘገባዎች እንዲሰሩ ግብዓት ሆኗል። ሕዝበ ውሣኔውን ለመዘገብ ፍላጎት ያላቸውን የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትን የመለየት፣ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርቡ ማስተባበር፣ አስፈላጊውን መረጃ አቅርበው ባጅ እንዲደርሳቸው ማድረግ:: በዚህም ሂደት ላይ ለመዘገብ ፍላጎት ላሳዩ ከቴሌቭዥን፣ ከኅትመት፣ ከሬዲዮና ከኦንላየን ሚዲያ ለተውጣጡ 17 መገናኛ ብዙኃን ዕውቅና የሰጠ ሲሆን፤ በሚዲያ ተቋሞቹ ለሚሠሩም 169 ዘጋቢዎች የዕውቅና ባጅ ተሰጥቷል።

ሕዝበ ውሣኔውን የተመለከቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትንና ጋዜጠኞች ተሳታፊ እንዲሆኑ ቦርዱ በይፋ በማህበራዊ ድህረገፅ ላይ ከሚያወጣው ጥሪ በተጨማሪ በኢሜል፣ ቴሌግራም እንዲሁም በስልክ ግንኙነት በመጋበዝ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

## 15. የስርዓተ ጾታና ማህበራዊ አካታችነት

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በስድስት ዞኖች እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች በተደረገው ህዝበ ውሣኔ የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ አካታችነትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ለመስክ አሰልጣኞች በተዘጋጀ ስልጠና ሴቶች ፤አካል ጉዳተኞች፤አረጋውያን፤ በቋንቋ እና በቁጥር አነስተኛ የሆኑ እና ልዩ ትኩረት የሚሹ ወገኖች በተመለከተ አካታችነት ላይ ያተኮረ እና የምርጫ አሰፈፃሚዎችን የአካታችነት ግንዛቤ የሚያሳድግ ስልጠና ተሰጥቷል ። ዜጎች በህግ የተቀመጡ መብቶቻቸውን አውቀው እንዲመዘገቡ እና ድምጻቸውን እንዲሰጡ በመገናኛ ብዙሀኖች ላይ የሚሰራጩ የአካታችነት መልእክትን የያዙ ማሰታወቂያ ስራዎች እንዲሰሩ የተደረጉ ሲሆን እነዚህም የማህበራዊ አካታችነት የሚዲያ መልእክቶች ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ ደካሞች፣ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ ዜጎች በምዝገባ እና በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ላይ ያላቸውን መብት ተረድተው እንዲሁም ስለ ህዝበ ውሣኔው ግንዛቤ ወስደው እንዲሳተፉ በምስል የተደገፉ የአንድ ደቂቃ ርዝመት ያላቸው የአካታችነት መልክቶች እንዲስራጩ ተደርጓል።

## 16. የመራጮች ምዝገባ

ቦርዱ ባወጣው የሕዝበ ውሣኔ አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመራጮች ምዝገባ በስድስት ዞኖችና በአምስት ልዩ ወረዳዎች ለሚኖሩ ማንኛውም ሕጋዊ መሥፈርቱን ለሚያሟሉ ዜጎች ክፍት ሆኖ ከታህሳስ 11 እስከ ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የተከናወነ ሲሆን፣ በተፈናቃይ ካምፕ ውስጥ ባሉ ልዩ ጣቢያዎች ላይ ደግሞ ከታህሳስ 22 እስከ ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሁም በመራጮች ምዝገባ ወቅት በቦርዱ የቁጥጥርና ክትትል ቡድን አማካኝነት የሕግ ጥሠት እንደተፈጸመባቸው ሪፖርት መደረጉን ተከትሎ የመራጮች ምዝገባ የተቋረጠባቸው ምርጫ ጣቢያዎች ከታህሳስ 26 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዳግም ምዝገባው ተካሄዶ በድምሩ በ**3,771** ምርጫ ጣቢያዎች ላይ **3,028,770** መራጮች ተመዝግበዋል። ከተመዘገቡት የመራጮች ቁጥር ውስጥ **1,453,399** የሚሆኑት ሴት መራጮች

ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ **1,575,371** መራጮች ደግሞ ወንዶች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ **493** የአካል ጉዳተኞች ይገኙበታል።

## 17. የመራጮች ምዝገባ ሂደት ክትትል

ቦርዱ የመራጮች ምዝገባ ሂደት በቦርዱ የአፈጻጸም መመሪያዎች መሰረት መከናወኑን የተመረጡ ምርጫ ጣቢያዎችን በማየት ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን በየጣቢያቸው መገኘታቸውን በማረጋገጥ፣ የአፈጻጸም ችሎታቸውን በመገምገም፣ የምዝገባ ሰነዶች አጠቃቀም ሁኔታ በተሰጠው ስልጠና መሰረት መከናወኑን በማመሳከር የክትትል ስራ የሚያከናውን ቡድን አሰማርቷል።

የዚህ የመራጮች ምዝገባ (VR) ሂደት የክትትል (Monitoring) ስራ የአጠቃላዩ የህዝበ ውሣኔ አፈጻጸም ክትትል (Referendum Processes Monitoring) አካል ሲሆን ከሚከናወነው የመራጮች ምዝገባ አንጻር የሚከተሉት አቅጣጫዎች ላይ በማተኮር የክትትል ስራው ተከናውኗል።

- የመራጮች ምዝገባ በመመሪያው  መሰረት መከናወኑን በመከታተል፣የአስፈጻሚዎች የስራ ብቃት ፣ የአፈጻጸም ችሎታ፣ የምዝገባ ሰነዶች አጠቃቀም ሁኔታ በተሰጠው ስልጠና መሰረት መከናወኑን ማረጋገጥ፣
- የምርጫ አስፈጻሚዎች ፤ የምርጫ ቁሳቁሶች እና ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን፤
- የምርጫ ጽ/ቤቶች የተቋቋሙበት ቦታ በህጉ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ እና ተገቢ የሆነ የፀጥታ ሀይል በየምርጫ ጣቢያው መመደቡን ማረጋገጥ እና ጉድለቶች አጋጥመው ከሆነም ቦርዱ ለሚወስዳቸው የማስተካከያ እርምጃዎች ጠቃሚ የሚሆን የመረጃ ግብአትን ማቅረብ ።
- በመራጮች ምዝገባ ሂደት የተከሰቱ ችግሮችን መለየት እና በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ወቅት ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ተገማች ችግሮች ከወዲሁ የመፍትሄ ሃሳቦችን በመፈለግ ለቦርድ ውሣኔ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ማጠናቀር ተጠቃሽ ስራዎች ነበሩ።

የክትትል ስራውን ለማከናወን ከአስራ አንዱም ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች የተወሰኑ ማእከላትን የተመረጡ ሲሆን እያንዳንዱ ማዕከል ካለው የጣቢያ ብዛት ውስጥ ከአምስት እስከ ሰባት በመቶ (5%-7%) የሚሆኑትን ጣቢያዎች በክትትል ስራው ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡ በዚህ መሰረት በጠቅላላው አንድ መቶ ሃምሳ አምስት (155) የሚደርሱ ጣቢያችን በናሙናው እንዲካተቱ በማድረግ የመራጮች ምዝገባ (Voters registration) የአፈጻጸም ሁኔታ በተዘጋጁት የክትትል ፎርሞች (Monitoring Tools) መሰረት የክትትል ስራው ተከናውኗል። ይህንን የክትትል ስራ ለማከናወን አምስት ቡድን ተዋቅሮ በእያንዳንዱ ቡድን ከሁለት እስከ ሶስት ባላሙያዎች ተሳትፈውበታል።

በመራጮች ምዝገባ የታዩ ከፍተኛ የህግ  እና የአሰራር ጥሰቶች፡-

- በግንባር መራጮች ሳይመጡ የመንደር ተጠሪ የሆነው ግለሰብ በሰጠው ዝርዝር መሰረት የምርጫ አስፈጻሚዎች መዝግበዋል።

- በምርጫ ጣቢያው ሰዎች እንደተመዘገቡ መዝገቡ የሚያሳይ ሲሆን ነገር ግን በመራጮች ስም ዝርዝር ትይዩ የግለሰቦቹ ፊርማ የለም።
- የምርጫ አስፈጻሚ ያልሆነ እና የቀበሌ አመራር የሆነ ሰው በምርጫ ጣቢያው የአስፈጻሚ ገዋን ለብሶ መራጮችን ሲመዘግብ የተገኘ መሆኑ
- ለመራጭ በተሰጠው ካርድ እና በተመዘገበው ፊርማ መካካል ከፍተኛ ልዩነት ማሳየቱ
- አንድ ሰው የፈረማቸው የሚመስሉ ለተለያዩ ሰዎች የተፈረሙ ፊርማዎች ታይተዋል።
- ከ18 ዓመት በታች የሆኑ እና የአካባቢው ነዋሪ መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ያልያዙ ተማሪዎችን የመመዝገብ ስራ መሰራቱ ናቸው።

ከዚህ በላይ በተደረገው ሰፊ የክትትል ሥራ ከመራጮች ምዝገባ አንጻር ከፍተኛ የአሠራር ግድፈቶች እንዲሁም የሕግ ጥሠቶች መኖራቸውን ለመለየት የተቻለ ሲሆን፤ ቦርዱም በዚህ ጉዳይ ላይ ፈጣን ውሣኔ በማሳለፍ አስፈላጊውን የማስተካከያ ዕርምጃ ወስዷል። በቦርድ አመራሮች ጭምር የተመራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማስተካከያዎችና የተለያዩ ውሣኔዎች ተወስደዋል። በተጨማሪም ዜጎች በምዝገባ እንዲሁም በድምፅ መስጠት ሂደቱ የታዘቧቸውን ግድፈቶች በቀጥታ ለቦርዱ ለማሳወቅ እንዲችሉ በቀረቡ ነፃ የስልክ ጥሪ መስመሮች አማካኝነት በደረሱት ጥቆማዎች መሠረት የተለያዩ የማስተካከያ ዕርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን፤ መረጃዎችን የመስጠት ሥራም እንዲሁ ተሠርቷል።

በዚሁ መሠረት በመራጮች ምዝገባ ወቅት 24 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ በቦርዱ የቁጥጥርና ክትትል ቡድን አማካኝነት በተደረገ ክትትል የሕግ ጥሠት ተፈጽሞባቸው በተገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተካሄደው የመራጮች ምዝገባ እንዲሠረዝና ዳግም የመራጮች ምዝገባ እንደ አዲስ የተደረገ ሲሆን፤ የምርጫ አስፈጻሚዎቹም በአዲስ እንዲተኩ ተደርጓል። በሕግ ጥሠቱ የተሣተፉ አስፈጻሚዎችና የአስተዳደር አካላትም በፌደራል ፖሊስ ምርመራ እየተደረገባቸው ይገኛል። በተጨማሪም በሕጉ የምርጫ ጣቢያዎች መሆን እንደሌለባቸው በተደነገጉ በታዎች ላይ የተከፈቱ ጣቢያዎችን በመለየት ተለዋጭ ጣቢያዎች የተከፈቱ ሲሆን፤ የፀጥታ አካላት ባልተመደቡባቸው በታዎችም የፀጥታ አካላት እንዲሟሉ ተደርጓል።

## 18. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተመለከተ

ቦርዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች በሕዝበ ውሣኔው የሚሣተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሲሠራ የቆየ ሲሆን፤ በሁለት ዞኖችና በሦስት ልዩ ወረዳዎች ላይ ማለትም በኮንሶ ሦስት ምርጫ ጣቢያዎች፣ በጋሞ ሁለት ምርጫ ጣቢያዎች ፣ በአሌ ሶስት ጣቢያዎች እና በዲራሼ አንድ ምርጫ ጣቢያ በድምሩ ዘጠኝ ልዩ ምርጫ ጣቢያዎችን በተፈናቃይ ማቆያ ካምፕ ውስጥ አቋቁሞ የመራጮች ምዝገባ በማከናወን ድምፃቸውን እንዲሰጡ አድርጓል።

## 19. የድምጽ አሰጣጥ

ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም. የተካሄደው ድምፅ የመስጠት ሂደት የፀጥታ ችግር ያልታያበት ፣ በጥቂት ምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ወረቀት እጥረት ያጋጠመበት እና ችግሮቹ ወዲያውኑ የተፈቱበት የቦርድ አመራር አባላት እና 13 ከቦርዱ የተላኩ የክትትል ቡድኖች የመሥክ ጉብኝቶችን ያደረጉበት ፤ የድምፅ ቆጠራውም በዕለቱ ተጠናቆ በየምርጫ ጣቢያዎቹ ውጤቱ የተለጠፈበት ቀን ነበር። በድምጽ መስጫው እለት

ከመራጮች የሚመጡ ጥቆማዎችን መሠረት በማድረግ የተለያዩ የማስተካከያ ዕርምጃዎች ሲወስዱ ውለዋል።

### 20. የምርጫ ውጤት ማሰባሰብ

ቦርዱ ጥር 29 ቀን 2015 ዓ/ም ባካሄደው ህዝበ ውሣኔ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ በልዩ ወረዳዎች ፣ በዞኖች ጊዜያዊ ውጤት ይፋ ተደርጓል። ከዚሁ ቀን ጀምሮ የማእከል አስተባባሪዎች ከምርጫ ጣቢያ የመጣውን ውጤት ሊዳመር የሚችል እና ሊዳመር የማይችል በማለት እንዲለዩ ተደርጓል። በተጨማሪም በዞን እና በልዩ ወረዳዎች የህዝበ ውሣኔውን ውጤት የማረጋገጥ እና የማዳመር ስራ ተከናውኗል። ከቦርዱ የሄደው የክትትል ቡድንም በዞን እና በልዩ ወረዳዎች ላይ የማዳመሩ ስራ ላይ እገዛ አድርጓል። በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ከተማ በሚገኘው የሕዝበ ውሣኔው ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ውጤቶችን የማጣራትና የማረጋገጥ ሥራ የተሰራ ሲሆን ይህን የስራ ሂደትም በቦርዱ ዕውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎችና የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች በቦታው በመገኘት እንዲታዘቡና እንዲዘግቡ ይፋ በመደረጉ የመታዘብና የመዘገብ ስራ ተሰርቷል

### 21. የህዝበ ውሣኔ ውጤት

ቦርዱ በ6 ዞኖች እና በ5 ልዩ ወረዳዎች ተዳምሮ የመጣውን ውጤት በመመርመር እና በማረጋገጥ የዎላይታ ዞን በጠቅላላው እና በሌሎች ዞን እና ልዩ ወረዳዎች የ81 ጣቢያዎችን ውጤት ሳይጨምር እና ሳያካትት የሌሎቹን ውጤቶች አጽድቆ ይፋ አድርጓል። ይህም ውጤት በተጠቃለለው የውጤት መግለጫ ላይ ተካቷል።

## የሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሣኔ አፈጻጸም

### 1. በዎላይታ ዞን ህዝበ ውሣኔ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጡ ውሣኔዎች

በዎላይታ ዞን በውጤት ማረጋገጥ እና ማመሳከር ወቅት፣ የ77 ጣቢያዎች የውጤት ማስታረቂያ እና መግለጫ ቅፆች ግድፈቶች ስለታየባቸው የጣቢያዎቹ የመራጮች መዝገቦች ማጣራት እንዲደረግባቸው ቦርዱ ትዕዛዝ አስተላልፏል ። በዚሁ ትእዛዝ መሰረት ከ77 መዝገቦች ውስጥ በ74ቱ የመራጮች መዝገቦች ባልተጠበቀ መልኩ መጠነ ሰፊ የህግ ጥሰቶች በመገኘታቸው ቦርዱ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ወሰነ።

በውሣኔው መሰረት በዎላይታ ዞን ከተደራጁት ስምንት ማዕከላት ውስጥ ከሚገኙት **1,112** የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ለምርመራው ከእያንዳንዱ ማዕከላት **25%** ጣቢያዎች ማለትም **የ277** ምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች መዝገቦች በናሙናነት ተወስደው ምርመራ ተደርጎባቸዋል። ከተመረመሩት ጠቅላላ **350** መዝገቦች ውስጥ የተፈፀመባቸው ጥሰት አስር እና ከዚያ በታች በመሆኑ ሊታለፉ የሚችሉት **13** የመራጮች መዝገቦች ብቻ ሲሆኑ **337** መዝገቦች ግን ከፍተኛ የሆነ የህግ ጥሰቶች እና ግድፈቶች እንዳለባቸው ተረጋግጧል።

በተጨማሪም የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የክትትል ቡድኖች በ**10** የምርጫ ጣቢያዎች እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የምርጫ መብቶች ክትትል ቡድን በ**10** የምርጫ ጣቢያዎች የተለያዩ ጥሰቶች ማለትም (ከ18 ዓመት በታች ያሉ ዜጎች ድምፅ መስጠታቸው፣ ለሌላ ሰው መምረጥ፣ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ማጨቅ፣ ሚስጥራዊነትን መጣስ፣ የታዛቢነት ባጅ ሳይኖራቸው በምርጫ ጣቢያ ታዛቢነት መገኘት) መፈፀማቸውን አረጋግጠዋል። በዚህም መሰረት የዎላይታ ዞን ህዝበ ውሣኔ የመራጮች ምዝገባ ውድቅ እንዲደረግ እና የመራጮች ምዝገባ እና ድምፅ አሰጣጡም በድጋሚ እንዲደረግ ቦርዱ ወስኗል።

በዎላይታ ዞን የተካሄደው የሕዝበ ውሣኔ በመራጮች ምዝገባና በሕዝበ ውሣኔው ቀን በታዩ ጉልህ የሕግ ጥሠቶች ላይ ቦርዱ የዞኑን ውጤት ውድቅ በማድረግና የተፈጸመው የሕግ ጥሠት ላይ የፍትህ ሚኒስቴር እና ፌደራል ፖሊስ ምርመራ እንዲያደርግበት ደብዳቤዎች ጽፏል ። ቦርዱ የፍትህ ሚንስቴር እና የፌደራል ፖሊስ ከክልሉ ፍትህ ቢሮና ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመተባበር አጥፊዎች ላይ እርምጃ መውሰድ መጀመሩንም በማረጋገጥ የዳግም ህዝበ ውሣኔውን የማስፈጸም ስራ ሊጀምር ችሏል።

## 2. የወንጀል ጥሰትን በተመለከተ የተደረገ ክትትል

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በ6 ዞኖችና 5 ልዩ ወረዳዎች ህዝበ ውሣኔ ተካሂዶ የነበረ ቢሆንም በዎላይታ ዞን ከተቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 357 ጣቢያዎች ሰፊ የሆነ የምርጫ ህግ ጥሰት ተፈፅሞባቸው የነበረ በመሆኑ ጉዳዩ የወንጀል ምርመራ እንዲደረግበት ቦርዱ ጉዳዩን ለፖሊስ መርቷል። በዚህ ሂደት የወንጀል ጉዳይ ተጠያቂነትን በተመለከተ የህግ ክፍል ለፖሊስና ለዓቃቤ ህግ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመስጠት የወንጀል ተጠያቂነት ሂደቱን በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

በፍትህ ሚኒስቴር ሪፖርት መሰረት 136 ተጠርጣሪዎች የተለዩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 18ቱ በወቅቱ የምርጫ አስፈጻሚዎችን በማስገደድ በመደለል እና በማሰፈራራት የምዝገባ እና የምርጫ ሂደት ላይ ጥሰት ፈጽመዋል በሚል የተጠረጠሩ የቀበሌ አመራሮች እና የወረዳ ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ሲሆኑ ቀሪ 118ቱ የምርጫ አስፈጻሚዎች ናቸው። በአጠቃላይ 94 ተጠርጣሪዎች የተያዙ ሲሆን 76 ተጠርጣሪዎች ከምርጫ አስፈጻሚዎች 18 ተጠርጣሪዎች በወቅቱ የምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ቀን የምርጫ ህግ ጥሰት ፈጽመዋል በሚል የተጠረጠሩ የቀበሌ አመራር ናቸው።

## 3. እቅድ ዝግጅት

ቦርዱ ሕዝበ ውሣኔው ሕጉን ጠብቆ ዳግም እንዲካሄድ የጊዜ ሰሌዳ አወጣ። በዚህም የጊዜ ሰሌዳ ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. የመራጮች ምዝገባውና የድምፅ አሰጣጡን በአንድ ቀን ለማከናወን ዐቅዶ ወደ ሥራ ገብቷል። ከዕቅድ ዝግጅትም አንጻር ለመራጮች ምዝገባ እና ለድምፅ አሰጣጥ ቁሳቁሶችን የማዘጋጀት ሥራዎች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ፣ ምደባ እና ስምሪት ፣ አጠቃላይ የሎጀስቲክስ ዝግጅትና የሥምሪት ሥራዎች ፣ ከፀጥታ አካላት ጋር፣ የኮሚኒኬሽን ሥራዎች፣ የሥነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ሥራዎች፣

የታዛቢዎች ሥምሪትና የውጪ ግንኙነት ሥራዎች እንዲሁም የበጀት ዝግጅትና ሌሎች ለሕዝበ ውሣኔው ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በሙሉ የተካተቱበትን ዕቅድ በማውጣት ቦርዱ እንዲያፀድቀው ተደርጓል።

## 4. የድጋሚ ህዝበ ውሣኔ ጽ/ቤቶች ማደራጀት

ቦርዱ በዎላይታ ዞን የድጋሚ ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈጸም እንዲሁም ሕዝበ ውሣኔውን በተሳካና በተቀናጀ አሠራር ለማከናወን እንዲቻል፤ ለሕዝበ ውሣኔው ማስፈጸሚያነት የሚያገለግል ጊዜያዊ ጽ/ቤት በዞኑ ያቋቋመ ሲሆን፤ በሥሩም ከዚህ በፊት በዞኑ በነበሩት ስምንት ማዕከላት ላይ አራት ማዕከላትን በመጨመር በድምሩ 12 የሕዝበ ውሣኔ ማስተባበሪያ ማዕከላት አደራጅቷል። ከላይ እንደተገለጸው በዎላይታ ዞን በተካሄደው ሕዝበ ውሣኔ ላይ የተፈፀሙ የሕግ ጥሠቶችን እና የማጭበርበር ሁኔታዎች ዳግም እንዳይፈጸሙ ለመከላከል የድጋሚ ሕዝበ ውሣኔው የመራጮች ምዝገባና የድምፅ አሰጣጥ ሂደት በአንድ ቀን እንዲሆን ወስኗል። የምዝገባው ቀንና የምርጫው ቀን አንድ ቀን በመሆኑ ምክንያት የምርጫ ጣቢያዎች መጨናነቅና በመራጩ ላይም እንግልት እንዳይፈጥር፤ በአንድ ምርጫ ጣቢያ በአማካኝ የሚያስተናገደው 1,500 የነበረውን የመራጮች ቁጥር ወደ 800 ዝቅ እንዲል ተደርጓል። ይህንንም ተከተሎ ከዚህ በፊት በነበሩት ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ተጨማሪ 700 የምርጫ ጣቢያዎች በመጨመር በድምሩ 1,812 የምርጫ ጣቢያዎች አደራጅቷል። በመሆኑም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ተጨማሪ ሦስት ማዕከላትን ጨምሮ 12 ማዕከላትንና መጋዘኖችን የማዘጋጀት እንዲሁም ለ1,812 የምርጫ ጣቢያ ጽ/ቤቶችን በዐዋጁ መሠረት ተገቢው ቦታ የመምረጥና የማዘጋጀት ሥራዎች ተከናውኗል።

## 5. ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ውይይት

ቦርዱ የሕዝበ ውሣኔው የኦፕሬሽን ዕቅድና የጊዜ ሠሌዳ በማዘጋጀት ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከክልሉ መንግሥት፣ ከዎላይታ ዞን የመስተዳድር አካላት እንዲሁም ከፌደራልና ከክልል ፀጥታ መ/ቤቶች ጋር የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ውይይት አድርጓል። በዋናነትም ከዞኑ የአስተዳደር አካላት ጋር ከአዲስ አበባ ለሚሄዱ የምርጫ አስፈጻሚዎች የመኝታ ቦታዎች ዝግጅት፣ በክፍያ የምግብ መስተንግዶ ስለሚሰጡ አካላት ዝግጅት፣ የምርጫ ጣቢያ ጽ/ቤቶች ዝግጅትና የተሽከርካሪ ድጋፍን በተመለከተ ውይይቶች የተደረጉ ሲሆን፤ በዚህም መሠረት ከዞኑና ከክልሉ መንግሥት 30 ተሽከርካሪዎችን በቦርዱ ወጪ የነዳጅና የሾፌር አበል በመቻል በትብብር ማግኘት ተችሏል። በተጨማሪም የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ከማዕከል ወደ ጣቢያ ለማድረስና ከምርጫ ጣቢያ ወደ ማዕከል ለመመለስ የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎችን ለማቅረብ ከዞኑ አስተዳደር ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት፤ ቦርዱ የትራንስፖርቱን ወጪ በዞኑ አስተዳደር የባንክ አካውንት በማስገባት ሥራዎችን ለማከናወን ተችሏል።

## 6. የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ

ሌላው የማጭበርበር ሂደቱን ለመከላከል በቦርዱ የተወሰደው እርምጃ በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ የተሣተፉና በሕዝበ ውሣኔው ላይ ለመሣተፍ ፍላጎት ያላቸውን የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ከአዲስ አበባ መልምሎ ማሳተፍ ነበር። በዚህም መሠረት ለሕዝበ ውሣኔው ከሚያስፈለጉ 9,060 አስፈጻሚዎችን ውስጥ 5,436ቱን ከአዲስ አበባ መልምሏል። ቀሪ 3,624ቱን ደግሞ ከዎላይታ ዞን እንዲሆኑ በማድረግ ውል

ፈጽመው ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል። ከዚህ በፊት በዎላይታ ዞን የሠሩት አስፈጻሚዎችን ሙሉ በሙሉ በመቀየር የቦርዱን ገለልተኝነት ለማስጠበቅ ተችሏል። ከአዲስ አበባ የተመለመሉት ምርጫ አስፈጻሚዎች ከአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ወደ ዎላይታ ዞን ለማጓጓዝም 99 አውቶብሶችን ተጠቅሟል።

ሕዝበ ውሣኔውን በዞን ደረጃ የሚያስተባብሩና የሚከታተሉ አምስት ባለሙያዎች የተሠማሩ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ ሁለቱ ከቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት፣ አንዱ ከዚህ በፊት በዞን ደረጃ ሲሠሩ ከነበሩት የዞን አስተባበሪዎች መኻል የተመረጠ እንዲሁም ቀሪ ሁለቱ ደግሞ ከማዕከላት አፈጻጸማቸውንና ገለልተኝነታቸውን በመገምገም የተመደቡ ናቸው። የሕዝበ ውሣኔው ማዕከላቱ ከአራት እስከ ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴዎች እንዲኖራቸው ተደርጎ ተደራጅተዋል። በመሆኑም በአጠቃላይ 62 የሕዝበ ውሣኔ ማዕከላት አስተባባሪዎች ተመርጠው በ12ቱም የሕዝበ ውሣኔ ማዕከላት እንዲሠማሩ ተደርጓል።

## 7. የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና

በምርጫ አስፈጻሚነት የሚሳተፉ አካላት፤ የምርጫ ህጉን በአግባቡ እንዲረዱ፤በምርጫ ተግባራት ላይ ስለሚኖራቸው ሚና፤ እና የመራጮች ምዝገባ ሂደት፤ እንዲሁም የድምጽ አሳጣጥ ውጤት ቆጠራ እና ይፋ አደራረግ ላይ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው፤ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚያስችሉ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

በዚህም መሰረት የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና በወላይታ በ12 እና በአዲስ አበባ በ5 የስልጠና ማእከላት ተካሂዷል። በወላይታ የተሰጠው ስልጠና ከግንቦት 23-28 ቀን በ2 ዙሮች የተሰጠ ሲሆን፤ በተጨማሪም ለተጠባባቂ የምርጫ አስፈጻሚዎች ሰኔ 7 እና 8 ቀን 2015ዓ.ም ስልጠና ተሰጥቷል። በዚህም መሰረት በወላይታ በድምሩ 3,988 የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠናውን ወስደዋል። እንዲሁም በአዲስ አበባ ከሰኔ 2-7 ቀን 2015ዓ.ም ድረስ በ2 ዙሮች ስልጠናው ተሰጥቷል። በዚህም በድምሩ 5,252 የምርጫ አስፈጻሚዎች በስልጠናው ላይ ተሳትፈዋል። በአጠቃላይ ተጠባባቂዎችን ጨምሮ በወላይታ ዞን እና በአዲስ አበባ 9,246 የምርጫ አስፈጻሚዎች በስልጠናው ተሳትፈዋል።

## 8. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

ቀደም ሲል ቦርዱ ሕዝበ ውሣኔ የሚመራበትን መመሪያ አውጥቶ የነበረ ሲሆን፤ የቅሬታ ሰሚ አደረጃጀትን በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 19/2015 አንቀጽ 11 መሠረት የቅሬታ ሰሚ

ኮሚቴ የተደራጀው በዞንና በልዩ ወረዳ ብቻ የነበረ መሆኑ የአፈጻጸም ክፍተት ስለነበረው እንዲሁም የተፈጠረውን ሰፊ የሕግ ጥሠት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና ቅሬታ አቅራቢ የሆነ ሰው በቅርበት ቅሬታውን የሚያቀርብበትን ሁኔታን ለማመቻቸት በማሰብ፤ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በተሻለ ቅርበት በ12ቱም የሕዝበ ውሣኔ ማዕከላት ጽ/ቤት እንዲሆን በመመሪያ ቁጥር 19/2015 ላይ ማሻሻያ ቀርቦ ፀድቋል። በማሻሻያውም መሠረት የቅሬታ ሰሚው ኮሚቴ አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ ከሕግ ክፍሉ እንዲያገኝ ተደርጎ ተደራጅቶና ከቦርዱ ጋር ውል ገብቶ፤ በዞንና በማዕከል የሕዝበ ውሣኔ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንዲቋቋም ተደርጋል።

ሕዝበ ውሣኔው በሰላም እንዲጠናቀቅም በምርጫ ነክ ወንጀሎችና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያም የክልሉን እንዲሁም በዎላይታ ዞንና በሥሩ ላሉ ወረዳዎች የፖሊስ አባላት ጭምር ዐቅማቸውን ማጎልበት የሚያስችል ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ የፖሊስ አባላቱ ምርጫ ነክ ወንጀሎችን በአፋጣኝ መርምሮ ለሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ በማቅረብ ‘ረገድም የሚጠበቅባቸውን ተግባራትና ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጡ ለማስቻልም ለ53 የፖሊስ አባላት በዎላይታ ሶዶ ከተማ ሥልጠና ሰጥቷል።

## 9. ቁሳቁስ ግዥ፣ ድልድል እና ስርጭት

ቦርዱ ለድጋሚ ሕዝበ ውሣኔው የመራጮች ምዝገባና ለድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የሚያገለግሉ የጽሕፈት መሣሪያዎችን የያዙ ኪቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ ካርድና የተለያዩ በድምፅ መስጫ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቅጾች ግዢ ከነመጠባበቂያው ለ1,812 ምርጫ ጣቢያዎች የሚሆኑ ጣት ላይ የሚቀቡና የማይጠፉ ቀለማት እንዲሁም የ1,804,000 የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ግዢ ከዱባይ ተፈጽሟል። በጠቅላላው ለሥልጠናና ለምርጫ ኦፕሬሽን የዋሉ ኅትመቶችና ኪቶች ግዢ የዋለው የገንዘብ መጠን ብር 19,028,922.80 (አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ኻያ ስምንት ሺ ዘጠኝ መቶ ኻያ ሁለት ብር ከሰማንያ ስንቲም) ሆኗል።

በሕዝበ ውሣኔው 1,812 ምርጫ ጣቢዎች አገልግሎት ላይ የሚውሉ ለመራጮች ምዝገባ፣ ለድምፅ አሰጣጥ ሂደት፣ ለውጤት ማዳመሪያ፣ ለሥልጠናና ለኦፕሬሽን አገልግሎት የሚውሉ ሠነዶችና ቁሳቁሶችን እንዲሁም የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ጨምሮ ሌሎች ቁሳቀሶች በተገቢው መንገድ ከነመጠባበቂያው በማሸግ ከተሟላ እጀባ ጋር በ12ቱም የሕዝበ ውሣኔው ማስተባበሪያ ማዕከላት የማሠራጨት ሥራ ተሠርቷል። የእሽጋና የሥርጭት ሥራውም በሦስተኛ ወገን ሠራተኞች (ከቦርዱ የሎጅስቲክ ሠራተኞች ጋር በመቀናጀት) ተከናውኗል። የሠነድ ሥርጭቱ ቦርዱ በኪራይ ባመጣቸው 32 ተሽከርካሪዎችና 30 ከአስተዳደር አካላት በተገኙ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች በመጠቀም ከሰኔ 9 እስከ ሰኔ 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ የማሠራጨት ሥራ ተሠርቷል።

## 10.የውጭ ግንኙነት

በቦርዱ የውጭ ግንኙነት የሥራ ክፍል አማካኝነት በዎላይታ ዞን የድጋሚ ሕዝበ ውሣኔ ላይ በታዛቢነት የሚሣተፉ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶችን መለየት፣ ለመታዘብ ከተለዩት ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ተወካዮች ጋር የቅድመ ሕዝበ ውሣኔ የምክክር መድረክ ማዘጋጀትና ማከናወን፣ የተመረጡት ሲቪል ማኅበራት እና ኢ.ሰ.መ.ኮ ለሚያሠማሩዋቸው ታዛቢዎችና የሰብዓዊ መብት ተከታታዮች ተንጠልጣይ ባጅ ማዘጋጀትና ማሠራጨት እንዲሁም በታዛቢነትና በሰብዓዊ መብት ተከታታይነት በመሥክ ለሚሠማሩ የሦስት ድርጅቶች፤ ማለትም ለኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ፣ ለኢ.ሰ.መ.ጉ እና ለኢ.ሰ.መ.ኮ የመሥክ አባላት አማካኝነት የሚሰጡትን የቅድመ ሥምሪት ሥልጠና በየቦታው በመገኘት ክትትል ማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቴክኒክ እገዛ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።
ሦስቱም ተቋማት 1ኛ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ 146 ታዛቢዎች፣ 2ኛ ኢ.ሰ.መ.ጉ 17 ታዛቢዎች እና 3ኛ ኢ.ሰ.መ.ኮ 7 የሰብአዊ መብት ተከታታዮችን አሰማርተው እንደቅድመተከተላቸው 117፤ 94፣ እና 27 በድምሩ 238 የምርጫ ጣቢያዎችን በእለቱ ሸፍነዋል።በዚሁ ቁጥር ልክ ተንጠልጣይ ባጅ ተዘጋጅቶ ተሰጥ□ል።

## 11.የሥነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት

በቦርዱ የሥነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ሥራ ክፍል አማካኝነትም አጫጭር የሕዝብ ማስታወቂያዎች (PSAs) በማዘጋጀት በቴሌቪዥንና በሬዲዮ እንዲተላለፉ ተደርጓል። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን በማሣተፍም በተለያዩ ወረዳዎች ላይ እየተዘዋወሩና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የመራጮች ትምህርትና መረጃ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል። በመሆኑም በሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መልዕክቶችን፤ ማለትም በዎላይታ ዞን ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. የሚካሄደውን የድጋሚ የሕዝበ ውሣኔ የተመለከተ የመራጮች መረጃን የሚሰጡ፣ በዎላይታ ዞን ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው ሕዝበ ውሣኔ ላይ የተፈጸሙትን የሕግ ጥሠቶች የተመለከቱና እንዲሁም ከሥርዓተ-ፆታና ከማኅበራዊ አካታችነት የሥራ ክፍል ጋራ በመሆን በአካታችነት ዙሪያ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉ፤ በአጠቃላይ ሦስት የድምፅ-ወ-ምሥል እንዲሁም ሦስት የድምፅ መልዕክቶች በማዘጋጀት በአራት የቴሌቪዥንና በሁለት የሬዲዮ ጣቢያዎች ላይ ለዐሥር ቀናት ለ194 ጊዜ እንዲተላለፉ ተደርጓል።

በመራጮች ትምህርት የአካታችነት መርኅን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻልና ሁሉም ዜጎች ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማድረግ እንዲሁም ሕዝበ ውሣኔው በሚካሄድበት ዞን የተደራሽነት ችግር ላለባቸው ማለትም ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ልዩ ትኩረት የሚሹ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሚገኙበት አካባቢ መሥራት ለሚፈልጉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፤ በውድድር ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የቀረበውን ጥሪ

ተከትሎ ላመለከቱ ሰባት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ለማበረታታት፤ ለሦስቱ ድርጅቶች ለ'ያንዳንዳቸው የ300,000 ብር ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፤ ለቀሪዎቹ አራት ድርጅቶች ደ'ሞ ለ'ያንዳንዳቸው የ250,000 ብር ድጋፍ ተደርጓል። ይህም ሲሆን ለሦስቱ ድርጅቶች የተሰጠው ድጋፍ ላይ የ50,000 ብር ጭማሪ ያሳየው፤ ከዚህ ቀደም በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም የተደረገውን ሕዝበ ውሣኔ በቦርዱም ሆነ በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ ሳይደረግላቸው በራሳቸው ጥረት የመራጮች ትምህርት የሰጡ በመሆናቸው ነው። ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ በሲቪል ማህበራት በብሬይል የተዘጋጀውን የአዋጅ ቅጾች እንዲሁም 44,000 በራሪ ወረቀቶች ታትመው ተሰራጭተዋል።

## 12.የኮሚዩኒኬሽን ስራዎች

በቦርዱ የኮሚኒኬሽን ሥራ ክፍል አማካኝነት የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ የአጫጭር የቴሌቪዥን መልዕክቶችን ስክሪፕት በማኅበራዊ ትሥሥር ገጽ ለማጋራት በሚያስችል መልኩ በመቀየር መልዕክቱን በምሥል ጭምር በመደገፍ መራጩን ሕዝብ፣ መገናኛ ብዙኃኑን፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና የአስተዳደር አካላትን ግንዛቤ እንዲያገኙ በማሰብ በማኅበራዊ ትሥሥር ገጽ ተጋርቷል። በምርጫ ዝግጅት ወቅት የተደረጉ ስብሰባዎችና መግለጫዎች ላይም መገናኛ ብዙኃኑ በዘገባ እንዲሣተፉ ለማድረግ በስልክ ጥሪ፣ በኢ-ሜል፣ አጭር የጽሑፍ መልዕክት በስልካቸው በመላክና በቦርዱ ማኅበራዊ ትሥሥር ገጽ ላይ ይፋዊ ጥሪ በማድረግ ጭምር እንዲገኙ ተደርጓል። በተጨማሪም ሕዝበ ውሣኔውን የተመለከተ የውይይት መድረክ ላይ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቭዥን፣ ከኅትመትና ከኦንላየን ሚዲያዎች የተውጣጡ 24 የመገናኛ ብዙኃን ተገኝተዋል። በጋዜጣዊ መግለጫዎችም ላይ እንዲሁ ቦርዱ ለምርጫ ዘገባ ልዩ ፍቃድ እንዲወስዱ ለሁሉም መገናኛ ብዙኃን ያቀረበውን ጥሪ ተከትሎ አመልክተው የዕውቅና ባጅ ያገኙና በቦርዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና የወሰዱ መገናኛ ብዙኃን አካላት ተገኝተው ዘግበዋል።

## 13.የምርጫ ዝግጅት እና የድምጽ አሰጣጥ ቀን

በቦርዱ ፀድቆ ተግባራዊ በተደረገው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት፤ የሕዝበ ውሣኔውን ተዓማኒነት ከፍ ለማድረግ እንዲሁም ገለልተኛነቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ በማሰብ በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ የተሻለ አፈጻጸም ያሳዩ ምርጫ አስፈጻሚዎችን ከአዲስ አበባ በመመልመልና በማሠልጠን በዞኑ በሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የመመደቡ ሥራ፣ የቁሳቀስ ግዢና ድልድል እንዲሁም ሥርጭት ሥራ፣ የተለያዩ የሕዝበ ግንኙነት አማራጮች በመጠቀም የመራጮች ትምህርት ሥራዎችን ማከናወን፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባና ሥምሪት እንዲሁም ሌሎች ለሕዝብ ውሣኔው አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መሟላታቸው ከተረጋጋጠ በኋላ ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. የዎላይታ ዞን የድጋሚ ሕዝበ ውሣኔ ተከናውናል። በድምፅ መስጫው ዕለትም ሁሉንም ምርጫ ጣቢያዎች ያካለለ የክትትል ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ በወቅቱ የተከሰቱ ችግሮችንም አፋጣኝ መፍትሔ በመስጠት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን ሰላማዊነት፣

ገለልተኛነትና ተዓማኒነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ የማስቀጠል ሥራ ተከናውኗል። ቦርዱ በተለያየ ምክንያት ከምሽቱ 12:00 በፊት ድምፅ መስጠት ያልቻሉ መራጮች በድምፅ መስጫው መጠናቀቂያ ሰዓት ሠልፍ ላይ መኖራቸውን በማረጋገጥና አንድም ሕጋዊ መሥፈርቱን ያሟላ የዞኑ ነዋሪ ድምፁን ሳይሰጥ እንዳይቀር በማሰብ የድምፅ መስጫውን ሰዓት እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት እንዲራዘም በመወሠን ተግባራዊ አድርጓል።

### 14.የዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የምርጫ ውጤት ማረጋገጥ፣ እና ይፋ ማድረግ

ቦርዱ በዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሣኔ ከ1,812 የምርጫ ጣቢያዎች የመጣውን ውጤት በመመርመር እና በማረጋገጥ የ25 ምርጫ ጣቢያዎችን ውጤቶች እንዲሰረዙ እና እንዳይዳመሩ በማድረግ የ **1,787** ጣቢያዎች ውጤት አጽድቆ ይፋ አድርጓል።

በመሆኑም በ **1,787** የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ፦

- ☞ በእለቱ የተመዘገበ እና በእለቱ ድምጽ የሰጠ መራጭ ብዛት ሴት **412, 953** ወንድ **425, 065** በድምሩ **838, 018** ነው።
- ☞ ዋጋ ያላቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ብዛት **791, 551** ሲሆን።
- ☞ ዋጋ አልባ የሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ብዛት ደግሞ **44, 756** ሆኖ ተመዝግቧል።

በዚሁ መሰረት :-

- ☞ በ6 ዞኖች ( ኮንሶ፣ዎላይታ፣ደቡብ ኦሞ፣ጋሞ፣ጎፋ፣ ጌዴኦ፣)እና የ 5 ልዩ ወረዳዎች (ቡርጂ፣ባሰኬቶ፣ አሌ፣አማሮ፣ዲራሼ) በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር **750, 254** ሲሆን
- ☞ በ6 ዞኖች ( ኮንሶ፣ዎላይታ፣ደቡብ ኦሞ፣ጋሞ፣ጎፋ፣ ጌዴኦ፣)እና የ 5ልዩ ወረዳዎች(ቡርጂ፣ባሰኬቶ፣አሌ፣ አማሮ፣ዲራሼ) በአንድ የጋራ

ክልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ **41, 297** ነው።

## የተጠቃለለ የህዝበ ውሣኔ ውጤት

ከዚህ በፊት የዎላይታን ህዝበ ውሣኔ ውጤት ሳያካትት የአምስት ዞኖች እና የአምስት ልዩ ወረዳዎች ብቻ የህዝበ ውሣኔ ውጤት አጸድቆ ለህዝበ ይፋ ያደረገ ሲሆን ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ/ም የዎላይታ የድጋሚ ህዝበ ውሣኔ በማከናወን የፌደሬሽን ምክር ቤት በጠየቀው መሰረት ሙሉ በሙሉ በስድስት ዞን እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች የተከናወነውን የህዝበ ውሣኔው ውጤቱን አጠቃሎ አቅርቧል።

በስድስት ዞኖች እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች በጥር 29 ቀን 2015 የተጠናቀቀው ህዝበ ውሣኔ እና ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ/ም የተከናወነው ህዝበ ውሣኔ በአጠቃላይ **4,471** የምርጫ ጣቢያዎች የተደራጁበት፣ **35** የህዝበ ውሣኔ ማእከላት የተቋቋሙበት እና **22,355** የምርጫ አስፈጻሚዎች የተሳተፉበት ነበር።

ጥር 29 ቀን የተከናወነው የህዝበ ውሣኔ የ81 የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት ከህግ ውጪ በሆነ አሰራር ምክንያት ከውጤቱ ያልተዳመሩ እና የተሰረዙ ሲሆን ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ/ም የተካሄደው የዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሣኔ **25** የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት ሳይዳመር እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ጥር 29 ቀን 2015 ዓ/ም የተከናወነው እና በቦርዱ የጸደቀው ህዝበ ውሣኔ እንዲሁም ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በዎላይታ የተከናወነው የድጋሚ ህዝበ ውሣኔ ውጤት ቦርዱ አጸድቆ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ይፋ አድርጓል፡፡

1) ***የኮንሶ*** *ዞን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***101, 114*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***1, 890*** *ነው፡፡*
2) ***የደቡብ ኦሞ*** *ዞን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***256, 159*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***5 364*** *ነው፡፡*
3) ***የዎላይታ*** *ዞን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***750, 254*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***41, 297*** *ነው፡፡*
4) ***የጋሞ*** *ዞን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***583, 757*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***9, 682*** *ነው፡፡*
5) ***የጌዴኦ*** *ዞን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***241 695*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***46, 749*** *ነው፡፡*
6) ***የጎፋ*** *ዞን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***243, 327*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***12, 306*** *ነው፡፡*
7) ***የቡርጂ ልዩ ወረዳ*** *በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***28, 460*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***765*** *ነው፡፡*
8) ***የባስኬቶ ልዩ ወረዳ*** *በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***27, 674*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ከልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***1, 133*** *ነው፡፡*

9) ***የአሌ ልዩ ወረዳ*** *በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***22, 395*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***412*** *ነው።*

10) ***የአማሮ ልዩ ወረዳ*** *በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***90, 377*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***216*** *ነው።*

11) ***የዲራሼ ልዩ ወረዳ*** *በአንድ የጋራ ክልል መደራጀት እደግፋለሁ ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር* ***51, 467*** *ሲሆን በአንድ የጋራ ክልል መደራጀትን አልደግፍም ብለው ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር ደግሞ* ***453*** *ነው።*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የህዝበ ውሳኔ ውጤት ማሳወቂያ

| ህዝበ ውሳኔው የተካሄደበት ዞን/ልዩ ወረዳ | የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት | የተመዘገቡ መራጮች ብዛት | | | ድምፅ የሰጡ መራጮች ብዛት | | | በውጤቱ ያልተካተቱ የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት | የምርጫ ቀን የድምፅ መስጠት ተሳትፎ (Voter Turnout) | ዋጋ አልባ ድምፆች | ዋጋ ያላቸው ድምፆች | የህዝበ ውሳኔ ምርጫ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | | | | | አርግብ | ጎጆ |
| ኮንሶ ዞን | 135 | 57,753 | 53,808 | 111,561 | 54,760 | 50,532 | 105,292 | 4 | 94% | 2,180 | 103,004 | 101,114 | 1,890 |
| ደቡብ ኦሞ ዞን | 428 | 144,056 | 153,892 | 297,948 | 129,392 | 137,599 | 266,991 | 4 | 90% | 5,273 | 261,523 | 256,159 | 5,364 |
| ወላይታ ዞን | 1,812 | 412,953 | 425,065 | 838,018 | 412,953 | 425,065 | 838,018 | 25 | - * | 44,756 | 791,551 | 750,254 | 41,297 |
| ጋሞ ዞን | 805 | 296,874 | 333,466 | 630,340 | 283,410 | 318,723 | 602,133 | 21 | 95% | 8,141 | 593,439 | 583,757 | 9,682 |
| ጌዴኦ ዞን | 626 | 176,472 | 196,282 | 372,754 | 139,941 | 161,053 | 300,994 | 23 | 80% | 11,941 | 288,444 | 241,695 | 46,749 |
| ጎፋ ዞን | 329 | 141,995 | 147,312 | 289,307 | 131,528 | 133,137 | 264,665 | 10 | 91% | 8,471 | 255,633 | 243,327 | 12,306 |
| ቡርጂ ልዩ ወረዳ | 39 | 17,273 | 18,850 | 36,123 | 15,604 | 14,339 | 29,943 | 2 | 83% | 676 | 29,225 | 28,460 | 765 |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 50 | 16,193 | 16,446 | 32,639 | 14,787 | 15,125 | 29,912 | 0 | 92% | 1,098 | 28,807 | 27,674 | 1,133 |
| አሌ ልዩ ወረዳ | 64 | 13,905 | 16,045 | 29,950 | 10,746 | 12,774 | 23,520 | 3 | 78% | 710 | 22,807 | 22,395 | 412 |
| አማሮ ልዩ ወረዳ | 98 | 46,441 | 47,792 | 94,233 | 44,808 | 46,574 | 91,382 | 7 | 97% | 598 | 90,593 | 90,377 | 216 |
| ዲራሼ ልዩ ወረዳ | 85 | 27,825 | 28,976 | 56,801 | 26,380 | 26,775 | 53,155 | 7 | 94% | 1,163 | 51,920 | 51,467 | 453 |

*ማስታወሻ: የወላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ መስጠት ሂደት በአንድ ቀን ስለተከናወነ የመራጮች ተሳትፎ አልተሞላም።

## ጥር 29 ቀን 2015 እና ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ/ም በተከናወነው ህዝበ ውሣኔ የታዩ እመርታዎች

ቦርዱ ከ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ከወሰዳቸው ትምህርቶች በመነሳት በርካታ የአፈጻጸም ሂደቶች ላይ ማስተካከያ ያደረገ ሲሆን እነዚህ የአሰራር ለውጦች በህዝበ ውሣኔው ሂደት ተግባራዊ እንዲደረጉ ሆነዋል፡፡ ይህም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እመርታዎች ሊመዘገቡ ችለዋል ፡፡

- ☞ በመራጮች ምዝገባ እና በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የክትትል ቡድኖች በማሰማራት እና የቅርብ ክትትል ስራዎች (Real Time Monitoring) በማድረግ በስራው ሂደት ከባድ የህግ ጥሰቶች እንዲሁም ቀላል የሚመስሉ ነገር ግን አሉታዊ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ክፍተቶችን በመለየት እና በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እና ውሣኔ እንዲሰጣቸው (Evidence Based Decision) በማድረግ ህዝበ ውሣኔውን ለመምራት የተቻለበት ሁኔታ ነበር ፡፡
- ☞ የምርጫ ሂደትን አካታችነት (Inclusiveness) ከማረጋገጥ አንፃር የመራጮችን መረጃ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በሁሉም የሕዝበ ውሣኔ ሂደት ቅጾች እና ሰነዶች የሴት እና የወንድ መራጮች አሀዝ ተለይቶ እንዲመዘገብ ፤ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች በህዝበ ውሣኔው የነበራቸው ተሳትፎን በተመለከተ መረጃው በተሻለ ሁኔታ ተሰብስቦ እንዲጠናቀር ተደርጓል፡፡
- ☞ በህዝበ ውሣኔው ተግባራት የስርዓተ ጾታ አካታችነት ( Mainstreaming) በተሻለ ደረጃ ተተግብሯል፤
- ☞ በቦርዱ አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 16 መሰረት ቦርዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች በህዝበ ውሣኔው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ልዩ ጣቢያ በማቋቋም ድምፅ እንዲሰጡ መደረጉ ትልቅ እመርታ ነው፡፡
- ☞ ቦርዱ በ6 ኛው ዙር ጠቅላላ የምርጫ የተሰተፉ ገለልተኛ የሆኑ አስፈጻሚዎችን የመረጃ ቋት በማዘጋጀት እና በየጊዜው በማሻሻል በየትኛውም ጊዜ ለሚከናወኑ ምርጫዎች ወይም ህዝበ ውሣኔዎች ዝግጁ ማድረግ መቻሉ ከዝግጁነት አንጻር እንደ አንድ አምርታ ሊነሳ የሚችል ሁነት ነው፡፡
- ☞ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በህግ የተሰጠውን በምርጫ ወቅት ሰብአዊ መብቶችን የመከታተል ሀላፊነት በአስቻይ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ በተቋማቱ መሀከል ተፈርሞ በኮሚሽኑ ስፋት ያለው የሰብአዊ መብት ክትትል ተፈፅሟል፡፡
- ☞ በዎላይታ ዞን የተካሄደው የህዝበ ውሣኔ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ በ1812 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ በአንድ ቀን መከናወኑ ችግር ከመፍታት አንጻር እና ሊፈጠሩ የሚችሉ የህግ ጥስቶች ከመከላከል አንጻር ቦርዱ ጠቃሚ ትምህርት የወሰደበት አፈጻጸም ነው፡፡
- ☞ በጥቂት ቀናት ውስጥ ቁጥሩ 9060 የሆነ ምርጫ አስፈጻሚ ከአዲስ አበባ እና ከዎላይታ መልምሎ እና ተገቢ የሆነ ስልጠና ሰጥቶ ለህዝበ ውሣኔ አፈፃፀም ዝግጁ ማድረግ፣ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ለተጓደሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ተጠባባቂዎችን በመያዝ በፍጥነት በመተካት የተደረገው ስራ ክፍተኛ መሻሻል የታየበት ነው፡፡

- ☞ 5,436 የምርጫ አስፈጻሚዎችን በ 99 (ዘጠና ዘጠኝ ) አውቶብሶች በተደራጀ እና በተናበበ ሁኔታ አሰፍሮ ወደ ህዝበ ውሣኔ ማእከላት በሁለት ሌሊቶች በማሰማራት በፊት ከነበሩ ልምዶች አንጻር ከፍተኛ የቅንጅት ስራ የታየበት አፈጻጸም ነበር፡፡
- ☞ የህዝበ ውሣኔው ሰኔ 12 ተከናውኖ ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ/ም ሁሉም የምርጫ ጣቢያ ቁሳቁሶች ወደ ማእከል **በአንድ ቀን** ብቻ እንዲሰባሰቡ ማድረግ መቻሉ እንዲሁም ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ/ም ከማእከል ወደ ዞን ሁሉም የምርጫ ውጤት እና ቁሳቁሶች **በአንድ ቀን** ተሰብስቦ እንዲገባ መደረጉ ትልቅ የአፈጻጸም ውጤታማነት የታየበት ነበር፡፡
- ☞ ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ/ም 5436 የምርጫ አስፈጻሚ ከምርጫ ጣቢያ ወደ ህዝበ ውሣኔ ማእከል **በአንድ ቀን** እንዲገቡ የማድረግ ስራ እና ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ/ም በ 99 አውቶብሶች ሁሉም የምርጫ አስፈጻሚ ወደ አዲስ አበባ ለመመልስ የተተገበረው የኦፕሬሽን እቅድ ስኬታማ ነበር፡፡
- ☞ ቦርዱ የክትትል ቡድን በ12 የህዝበ ውሣኔ ማእካለት በማሰማራት እንዲሁም 62ቱ የህዝበ ውሣኔ ማእካል ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ተሽከርካሪ ተመድቦላቸው እና የሚከታተሉት ምርጫ ጣቢያ ቁጥር ተወስኖላቸው ሂደቱን ክትትል ማድረጋቸው ፣ የነበሩ ችግሮች በወቅቱ ለውሣኔ ሰጪ አካላት እንዲደርሱ ማድረጋቸው ለምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ቴክኒካል ድጋፍ መስጠታቸው ትልቅ እመርታ ነው፡፡
- ☞ በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 161 ላይ የተፈለገውን ግዴታ ከመተግበር አንጻር በሁሉም ዘን እና ልዩ ወረዳዎች የታየው ምላሽ የሚያበረታታ እና ከበፊቱ አንጻር ሲታይ መሻሻል የተታየበት ነው፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦች

### 1. በመራጮች ምዝገባ ወቅት የታዩ ችግሮች

- ☞ በተወሰኑ ጣቢያዎች ላይ የወረዳ እና የቀበሌ አመራሮች በመራጮች ምዝገባ ወቅት አስፈጻሚዎች ህገወጥ የመራጮች ምዝገባ እንዲፈፅሙ ጫና ማሳደራቸው ፤
- ☞ ለመራጭነት ብቁ ያልሆኑ ዜጎች በመራጭነት ተመዝግበው መገኘታቸው እና በድምጽ በመስጠት ሂደት መሳተፋቸው (ምሳሌ፡- የመራጮች ካርድ ቤት ለቤት እየዞሩ ማደል፣ እድሜያቸው 18 ዓመት ያልደረሱ መራጮችን መመዝገብ)
- ☞ ቦርዱ የሕዝበ ውሣኔው ሁለቱም አማራጭ ለህዝብ በፍትሀዊነት የሚተዋወቁበትን እድሎች ቢፈጥርም ለሁለተኛው አማራጭ ቅስቀሳ የሚያደርጉ አካላት በበቂ ሁኔታ አለመሳተፋቸው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 2. በድምጽ አሰጣጥ እና ውጤት አገላለፅ

- ☞ በመራጮች ምዝገባ ወቅት እና በድምፅ መስጫ ቀን የተፈረሙ ፊርማዎች የተለያየ ሆኖ መታየት፤

በምዝገባ ወቅት በጽሑፍ ፊርማ የተፈረመ በድምፅ መስጫ ቀን በጣት አሻራ የተፈረመ የመራጮች ዝርዝር በመዝገቦቹ ላይ መታየቱ፤ለተለያዩ መራጮች (በምዝገባ ወቅትም፣ በድምፅ መስጫ ቀንም) አንድ ዓይነት ፊርማ ተፈርሞ መገኘቱ፤

- ☞ በመራጮች መዝገብ ላይ ከሚጠበቀው በላይ ብዛት ያለው የጣት አሻራ ምልክት (በመራጮች ምዝገባ ወቅትና በድምፅ መስጫ ቀን) የተደረገ መሆኑ፤
- ☞ በመራጮች መዝገብ ላይ የመራጮቹ መረጃ ተሞልተው ፊርማቸው በጽሑፍም ሆነ በአሻራ አለመሥፈሩ የሚጠቀሱ ናቸው።

## 3. በውጤት አደማመር፣ እና መረጃ አሞላል የነበሩ ችግሮች

- ☞ የውጤት ማሳወቂያ ቅጽ ላይ የማይፈቀዱ የዕርምት ሥራዎች መሠራቱና በሠነዶቹ ላይ ከፍተኛ ሥርዝ ድልዝ መታየቱ፤
- ☞ የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት፤ ከተመዘገቡና ድምፅ ከሰጡ መራጮችና ቁጥር ጋር አለመታረቅ፤
- ☞ በድምፅ መስጫ ቀን ድምፅ ለመስጠት ለተሠለፉ መራጮች ጊዜያዊ መታወቂያ ወረቀት በአካባቢ አስተዳደር አካላት መታደል፤
- ☞ ሚስጥራዊ ድምፅ መስጫ/መከለያ ውስጥ የአመራሮች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና ግለሰቦች አብሮ መግባት፤
- ☞ በድምፅ መስጫ ቀን አዲስ የመራጮች ምዝገባ ከበርዱ እውቅና ውጪ መደረግ ፤
- ☞ የምርጫ ጣቢያዎች መቋቋም በማይገባቸው ቦታዎች መቋቋማቸው ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።
- ☞ ብዛት ያላቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በአንድ ላይ ታጥፈው በድምፅ መስጫ ሣጥን ውስጥ ታጭቀው መገኘታቸው፣

## 4. በዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ ያጋጠሙ ችግሮች

- ☞ በዎላይታ ዞን በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች መራጮች የያዙት መታወቂያ የወጣበትን ቀን ስርዝ ድልዝ የተደረገበት እንዲሁም መታወቂያ የወጣበት ቀን ህዝበ ውሣኔው ከሚካሄድበት ቀን ከ 6ወር ያነሰ መሆኑ፣
- ☞ በዎላይታ ዞን አንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ እድሜያቸው ለመምረጥ ያልደረሱ ህጻናት ሰልፍ ላይ መገኘታቸው፣
- ☞ የቀበሌ አመራሮች ለእርግብ አማራጭ ድምጽ ጨምሩ በማለት የምርጫ አስፈጻሚዎቹ ላይ ጫና ማሳደራቸው፣

## የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ☞ በመራጮች ምዝገባ ወቅት የህግ ጥሰት በተፈጸመባቸው 24 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተካሄደው ምዝገባ ተሰርዞ በድጋሚ የመራጮች ምዝገባ እንዲካሄድ የተወሰነ ሲሆን ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተሳተፉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ውላቸው የተቋረጠ ሲሆን በህግ ጥሰት ወቅት ሚና የነበራቸው የአስተዳደር አካላትም እንዲጠየቁ ቦርዱ ለፌደራል ፖሊስ በደብዳቤ ጠይቆ በምርመራ ላይ ይገኛል፤
- ☞ የመራጮች ምዝገባ ሲጠናቀቅ ሪፖርት የተደረገባቸው እና በምርጫ ቀን በውጤት ማመሳከሪያ ቅጽ ላይ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር ልዩነት ባሳዩ ምርጫ ጣቢያዎችን መዝገቡን አምጥቶ በመመርመር ልዩነቱ ሊታለፍ ከሚችለው በላይ በሆነባቸው ምርጫ ጣቢያዎች ውጤቱ እንዲሰረዝ ተደርጓል፤
- ☞ ቦርዱ ፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና ሲቪል ማህበራት በድምጽ መስጫ ቀን ባደረጉት ክትትል እንዲሁም ቦርዱ የምርጫ ውጤት ትክክለኛነት በሚያረጋግጠበት ወቅት የተገኙ የህግ ጥሰቶችን በመመርመር፣ 81 የምርጫ ጣቢያዎች ውጤታቸው እንዳይካተት ተደርጓል።
- ☞ በዎላይታ ዞን የተካሄደው ህዝበ ውሣኔ ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዝ ተወስኖ ድጋሚ የህዝበ ውሣኔ ተካሂዷል።
- ☞ ህግ የጣሱ በአጠቃላይ 94 ተጠርጣሪዎች የተያዙ ሲሆን 76 ተጠርጣሪዎች ከምርጫ አስፈጻሚዎች 18 ተጠርጣሪዎች በወቅቱ የምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ቀን የምርጫ ህግ ጥሰት ፈጽመዋል በሚል የተጠረጠሩ የቀበሌ አመራሮች ናቸው።

## የበጀት አጠቃቀም

አጠቃላይ የህዝበ ውሣኔን ስራ ለማከናወን ተቋሙ በ2015 የነበረው የተስተካከለ በጀት ብር 470,421,770.50 (አራት መቶ ሰባ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ከ50/100) ብር ሲሆን ሰኔ 12 2015 የዎላይታ ድጋሚ ምርጫ ህዝበ ወሳኔ ከመከናወኑ በፊት የነበረው ቀሪ የህዝበ ውሣኔ በጀት ብር 157,111,837.07 (አንድ መቶ ሃምሳ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከ07/100) ነበር። ከዚህም ውስጥ ለዎላይታ ህዝበ ውሣኔ እስከ ሰኔ 26 ድረስ የመስክ አሰልጣኞች ስልጠና ፥ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዙር የምርጫ አስፈፃሚዎች ክፍያ ፥ የምርጫ ጣቢያ ለመከታተል ለሄዱ ሠራተኞች እንዲሁም ለፌደራል ፖሊሶች የምርጫ ቁሳቁስ ለሚያጅቡ የአበል እና የነዳጅ ፥ የመኪና ኪራይ ጨምሮ የተከፈሉ ክፍያዎች 109,865,255 ብር (አንድ መቶ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት

መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሳ አምስትብር) የደረሰ ሲሆን ይህም የዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሣኔ የበጀት አጠቃቀም እስካሁን 70% አድርሶታል። ከዚህም በተጨማሪ አገልግሎቱን አግኝተን ክፍያቸው ያልተፈፀመ እንዲሁም የምርጫ አስፈፃሚዎች ክፍያቸው ያልተፈፀመ ክፍያዎችን ጨምሮ 33,208,412 (ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስምንት ሺህ አራት መቶ አስራ ሁለት ብር) በርዱ በዚህ በጀት አመት መፈፀም የሚኖርበት ሲሆን በበጀት አመቱ መጨረሻ የተጠቃለለ ሪፖርት የምናቀርብ ይሆናል።

□□□□□ *1.* □□□ □□□□□□

| ዝርዝር | ወጪ እና ተከፋይ | በጀት |
|---|---|---|
| **የተስተካከለ የህዝበ ውሣኔ ጠቅላላ በጀት** | | **470,421,770.50** |
| **ጥር 29 ቀን 2015 ለተከናወነው ህዝበ ውሣኔ የተከፈለ** | **304,473,963.93** | |
| **ከሰኔ 12 ቀን 2015 የዎላይታ ድጋሚ ህዝበ ውሣኔ ጋር ተያይዞ ለልዩ ልዩ ወጪዎች የተከፈለ** | **109,865,255.00** | |
| **እስከ አሁን ያለተከፈሉ ነገር ግን አገልግሎት ያገኘንባቸው ቀሪ ክፍያዎች** | **33,208,412.00** | |
| **የተከፈለ እና የተከፋይ ድምር** | | **447,547,630.76** |
| **ቀሪ (ግምታዊ)** | | **22,874,139.74** |

በመሆኑም አጠቃላይ የህዝበ ውሣኔን በጀት ስንመለከት አጠቃላይ የህዝበ ውሣኔውን ስራ ለማከናወን የታቀደው የተስተካከለ በጀት ብር 470,421,770.50 (አራት መቶ ሰባ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ከ50/100) ብር ሲሆን አጠቃላይ የወጡ ወጪዎች እና ቀሪ ተከፋይን ጨምሮ ብር 447,547,630.76 (አራት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ከ76/100) ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ይህም ጥቅል ወጪ ከተስተካከለው በጀት አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙን 95.1% ያደረሰዋል።

## ምስጋና

በ ስድስት ዞን እና በአምስት ልዩ ወረዳዎች የተካሄደው ህዝበ ውሣኔ ስኬታማ ለማድረግ ቦርዱ ከተለያዩ አካላት፣ ተቋማት እና ግለሰቦች ትብብር አግኝቷል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለሚከተሉት ተቋማትና ግለሰቦች ምስጋናውን ያቀርባል።

- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣
- የፌደሬሽን ምክር ቤት፣
- በህዝበ ውሣኔው ለተሳተፉት የኮንሶ፥ ዎላይታ፥ደቡብ ኦሞ፥ጋሞ፥ጌዴኦ ፥ ጎፋ ዞኖች እና የቡርጂ፥ ባስኬቶ፥አሌ፥አማሮ፥ዲራሼ ልዩ ወረዳ መራጮች በሙሉ፣
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሃገር መከላከያ ሰራዊት ደቡብ እዝ ፣
- ለፌደራል ፓሊስ ኮሚሽን፣
- ለፍትህ ሚኒስቴር
- ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልልዊ መስተዳድር ጽ/ቤቶች
- ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ፓሊስ ኮሚሽን
- ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ለሰላም እና ጸጥታ ቢሮ,
- ለጋሞ፣ ለጎፋ፣ ለዎላይታ፣ ለጌዲዮ፣ለኮንሶና፣ ለደቡብ ኦሞ ዞኖች እና ለቡርጂ፣ለአማሮ፣ለደራሼ፣ ለባስኬቶ እና ለአሌ ልዩ ወረዳዎች መስተዳድሮች፣
- ለጋሞ፣ ለጎፋ፣ ለዎላይታ፣ ለጌዲዮ፣ለኮንሶና፣ ለደቡብ ኦሞ ዞኖች እና ለቡርጂ፣ለአማሮ፣ለደራሼ፣ ለባስኬቶ እና ለአሌ ልዩ ወረዳዎች የጸጥታ አካላት፣
- ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣
- ህዝበ ውሣኔውን በመታዘብ እና የመራጮች ትምህርት መስጠት ለተሳተፉ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች
- የተለያዩ እገዛን ላደረጉልን የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት (UNDP)፣ European Center for Electoral Support (ECES) እና IFES፣
- ለህዳሴ የአንደኛ ደረጃ የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት፣
- ለአዲስ ፓርክ ዴቬሎፕመንት እና ማኔጅመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
- ከመኖሪያ አካባቢያቸው ርቀው በመሄድ ባልተሟላ አንዳንዴም በአስቸጋሪ ሁኔታ ህዝበ ውሣኔውን ላስፈጸሙ የህዝበ ውሣኔው አስፈጻሚዎች እና ስራውን በማስተባበር ለደከሙ የቦርዱ ሰራተኞች።

-